# <u>በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተማሪዎች ምደባ</u>

## <u>የአፈፃፀም መመሪያ</u>

1. **አውጪ ባለሥልጣን፣**

የኢ.ፌ.ድሪ አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 10፣ 28 (7) እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ 650/2001 አንቀጽ 39፣ 92 (2) መሠረት ትምህርት ሚኒስቴር ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ</u>

2. **አጭር ርዕስ፣**

ይህ መመሪያ “በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተማሪዎች ምደባ የአፈፃፀም መመሪያ” ተብሎ ይጠቀሳል፡፡

3. **ትርጓሜ፣**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

3.1 **ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር** ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የትምህርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

3.2 **ኤጀንሲ** ማለት ሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ ማለት ነው፡፡

3.3 **ከፍተኛ የትምህርት ተቋም** ማለት እንደ አግባብነቱ በጀቱ በፌደራል ወይም በክልልና ከተማ አስተዳደር የሚተዳደር የከፍተኛ የትምህርት ተቋምና ሕጋዊ ፈቃድ /እውቅና/ አግኝቶ የተቋቋመ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው፡፡

ሳሙኤል ክፍሌ ኪዳኔ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

3.4 **መደበኛ ተማሪ** ማለት በትምህርት ሚኒስቴር ወይም በክልሎች እውቅና በተሰጠው መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ትምህርት ቤቶች በቀንና በማታ መርሃ ግብር ትምህርቱን የሚከታተል ተማሪ ማለት ነው፡፡

3.5 **የመሰናዶ ትምህርት** ማለት ከአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ በኋላ ለከፍተኛ ትምህርት ማዘጋጃ የሚሰጥ የሁለተኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት ማለት ነው፡፡

3.6 **የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግቢያ መመዘኛ ፈተና** ማለት የመሰናዶ ትምህርት ላጠናቀቁ ተማሪዎች የሚሰጥ ፈተና ነው፡፡

3.7 **ከፍተኛ የጤና ችግር ያለባቸው** ማለት በከፍተኛ ደረጃ የጤና መታወክ በመፈጠሩ ተከታታይ የህክምና ድጋፍ ሲያገኙ የቆዩና በቀጣይም ድጋፍ የሚፈልጉ መሆናቸውን በሕክምና ቦርድ የተረጋገጠ መረጃ የሚያቀርቡ ተማሪዎች ናቸው፡፡

3.8 **የአካል ጉዳተኛ** ማለት በደረሰባቸው የአካል ጉዳት ምክንያት በዊልቸርና በሁለት ክራንች የሚንቀሳቀሱ ተማሪዎች ብቻ ናቸው፡፡

3.9 **የትምህርት መስክ ምድብ** ማለት ለትምህርትና ለምደባ አገልግሎት እንዲያመች የተዘጋጀ የከፍተኛ ትምህርት የትምህርት መስኮች በጋራ የማደራጀትና የማቀናጀት አሠራር የሚያመለክት አደረጃጀት ነው፡፡

3.10 **ምደባ** ማለት ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲዎች መመደብ ነው፡፡

3.11 **ቅበላ** ማለት ወደ ከፍተኛ ትምህርት ሊያስመድብ የሚችል የማለፊያ ነጥብ ነው፡፡

ሳሙኤል ክፍሌ ኪዳኔ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

4. ዓላማ፣

በመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመቀበል አቅም እና በተማሪዎች ፍላጎትና ዝንባሌ መሰረት ግልፅና ፍትሃዊ የሆነና በውድድር እና በልዩ ድጋፍ ላይ የተመሰረተ የተማሪዎች ምደባ ለማከናወን ነው። በተጨማሪም በግል ወደ ከፍተኛ ትምህርት መግባት የሚችሉ ተማሪዎችን ውጤት ለመወሰን የሚያስችል ይሆናል፡ ፡

5. መሪህዎች

ግልፀኝነት

ዲሞክራሲያዊነት

ተጠያቂነት

ፍትሃዊነት

አገራዊ ፍላጎትና አቅም

6. አጠቃላይ ሁኔታዎች፣

6.1 በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት የመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ራሳቸው በቀጥታ ተማሪዎች ለመቀበል የሚችሉበት ጊዜ እስኪደርስ ሚኒስትሩ የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በማማከር የምደባ ሥራውን ለማከናወን የመግቢያ ፈተናውን በማስተዳደር ማለፊያ ነጥብና መግቢያ ነጥብ በመወሰን ስለ ልዩ ድጋፍ ተጠቃሚዎች መመሪያ በማውጣት ፣ የቅበላ ሥርዓት በመወሰንና የቅበላ አፈጻጸምን በመከታተልና በማስተካከል ላይ የተገደበ ሥራ ይሰራል።

6.2 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግቢያ ነጥብ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ መሰረት በማድረግ ፣ አገራዊ የማስተናገድ አቅምና በየአመቱ የሚመዘገበውን የተማሪዎች ውጤት ባገናዘበ ሁኔታ በትምህርት ሚኒስቴር ይወሰናል።

ሳሙኤል ክፍሌ ኪዳኔ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

## 7. የተፈጻሚነት ወሰን፣

7.1 ይህ መመሪያ ለትምህርት ሚኒስቴር ተጠሪ በሆኑ ሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና በዚህ መመሪያ ግዴታ በተጣለባቸው አስፈፃሚ አካላት፣የግል፣ የመንግስትና ኮሚኒቲ ትምህርት ቤቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የትምህርት መስክና ምደባ

## 8. ለምደባ ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች፣

8.1 የመሰናዶ ትምህርት ያጠናቀቁና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግቢያ የብቃት መመዘኛ ፈተና ወስደው የዘመኑ መቁረጫ ነጥቡን ያሟሉ፡፡

8.2 የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መመዘኛ ፈተና በድጋሚ የወሰዱ ተማሪዎች በዘመኑ ለግል ተፈታኞች በሚወጣው የመቁረጫ ነጥብ መሠረት የማለፊያ ነጥብ ያገኙ ይመደባሉ፡፡

## 9. በምደባና በቅበላ ወቅት አዎንታዊ ድጋፍ የሚደረግላቸው፣

ሁሉም ተማሪዎች ባስመዘገቡት ውጤት ተወዳድረው የሚገባቸውን የትምህርት መስክና የተቋማት ምርጫቸው የሚያገኙ ሲሆን፡-

9.1 ሴት ተማሪዎች /በቅበላና በምደባ ወቅት/፣

9.2 ዓይነስውራንና መስማት የተሰናቸው /በቅበላና በምደባ ወቅት/፣

9.3 የአካል ጉዳተኞች /በምደባ ወቅት/

9.4 ከፍተኛ የጤና ችግር ያለባቸውና በህክምና ቦርድ የተረጋገጠላቸው ተማሪዎች /በምደባ ወቅት/

9.5 ኢትዮጵያ ሱማሌ፣የአፋር፣ የቤንሻንጉል ጉምዝና የጋምቤላ ክልል ብሔር ብሔረሰቦች ተወላጆች በክልሉ ውስጥ የተማሩ /በቅበላ ወቅት/

9.6 በኦሮሚያና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ውስጥ የሚገኙ የአርብቶ አደርና ከፊል የአርብቶ አደር አካባቢ ነባር ብሔር ብሔረሰቦች /Indigenous/ ልጆች /በተወካዮች ምክር ቤት በተለዩ



ሳሙኤል ክፍሌ ኪዳኔ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

የአርብቶ አደር ወረዳዎችና ዞኖች/ተማሪዎች /በቅበላ ወቅት/ /ልዩ ትኩረትና ድጋፍ ይደረጋል፣

10.የኮሚኒቲ ባሕርይ ያላቸው ት/ቤቶችና በዜግነት ምክንያት ምደባ የሚታይላቸው፣

8.1 የኮሚዩኒቲ ት/ቤት ተማሪዎች ምደባ ከየትምህርት ቤታቸው በሚላከው ውጤት መሠረት በንፅፅርና በውድድር ሊመደቡ ይችላሉ፡፡

8.2 በዜግነት ኢትዮጵያውያን ያልሆኑ ሆኖም ማንኛውም ጥቅማ ጥቅም እንደ ኢትዮጵያዊ ዜጋ የማግኘት መብት ያላቸው ተማሪዎች ቢኖሩ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሚቀርበው መረጃ መሰረት የምደባው ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

8.3 በዜግነት ኢትዮጵያዊ ሆነው በውጭ ሀገር ተምረው ወደ ሀገራቸው የሚመለሱ ተማሪዎች የትምህርት ማስረጃቸው በአቻ ግመታ ተረጋግጦ የምደባ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

11.የትምህርት መስክና የተቋማት ምርጫ፣

11.1 የትምህርት መስክ በስድስት ምድብ ተደራጅቷል፡፡

11.1.1 የተፈጥሮ ሳይንስ የትምህርት ዘርፍ፣

Band 1- Engineering and technology
- (1a) Engineering sciences
- (1b) Computing sciences(Other than engineering sciences)
- (1c) Textile engineering

Band 2- 2a)Natural and Computational sciences
- 2b) Teachers Education in Natural Sciences

Band 3- Medicine and Health sciences
- (3a) Medicine
- (3b) Public Health Officer
- (3c) Other Health Sciences
- (3d) Dental Medicine

Band 4- Agricultural and Natural Resource Sciences
- (4a) Veterinary Medicine
- (4b) Other Agricultural & natural Resources sciences
- (4c) Veterinary Science



ሳሙኤል ክፍሌ ኪዳኔ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

11.1.2 ለማህበራዊ ሳይንስ የትምህርት ዘርፍ፣

Band 5- Business and Economics

Band 6- Social Sciences and Humanities

(6a) Law

(6b) Other Social Sciences & Humanities

(6c) Theatrical, Fine Arts and Music

(6d) Nation nationalities Language

(6e) Teachers Education in Social Sciences

11.2 የተቋማት ምርጫ፣

የየዓመቱን የመግቢያ መቁረጫ ነጥብ ያሟሉ ተማሪዎች ወደ መንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመመደብ በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በዝርዝር ተቀምጠው ሁሉንም በቅደም ተከተል ይመረጣሉ፡፡

12.ከፍተኛ የጤና ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ምደባ፣

10.1 በከፍተኛ የጤና ችግር ምክንያት ድጋፍ ሊደረግላቸው የሚገቡ ተማሪዎች በየመሰናዶ ትምህርት ቤቱ በኩል የተማሪው ሙሉ ስም የመለያ ቁጥር ተጠቅሶ የሜዲካል ቦርድ ሰርተፊኬት በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ፊርማና ማህተም ተረጋግጦ የትምህርት ቤቱ የድጋፍ ደብዳቤ ጭምር ውጤት በተገለፀ ባሉት 15 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለሀገር አቀፍ የፈተናዎች ኤጀንሲ መድረስ ይኖርበታል፣

10.2 መረጃው አጠራጣሪ ሆኖ ሲገኝ እና የሕመሙ ዓይነትና ደረጃ ለማወቅ ሲፈለግ የሚመለከታቸው የጤና ባለሙያዎችን የማማከር ስራ ይሰራል፣

10.3 ከፍተኛ የጤና ችግር ኑሮባቸው የህክምና ክትትል የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች የህክምና ጤና ተቋማት ባላቸው ዩኒቨርስቲዎች ይመዳባሉ፣



ሳሙኤል ክፍሌ ኪዳኔ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

10.4 የምደባ ውጤት ከታወቀ በኋላ የሚቀርብ ማንኛውም የሕክምና መረጃ ተቀባይነት የለውም፣

10.5 የጤና መረጃው ሐሰተኛ ሆኖ በተገኘበት ወቅት ትምህርት ቤቱም ሆነ ተማሪው ባለው ሕግ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡ በዚህ መረጃ የተገኘ ምደባው ይሰረዛል፣

## ክፍል ሶስት

13. ይህንን መመሪያ በማስፈፀም ሂደት የልዩ ልዩ አካላት ኃላፊነትና ግዴታ፣

13.1 ትምህርት ሚኒስቴር፣

ሀ/ የተማሪዎች ምደባ መመሪያ ያወጣል፣ ያሻሽላል፣ ለክልል ትምህርት ቢሮዎችና ለዩኒቨርስቲዎች መመሪያውን ያስተዋውቃል ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፣

ለ/ ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚያስገባ ነጥብን ይወስናል፣

13.2 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣

ሀ/ ዩኒቨርሲቲዎች የ5 አመት የመቀበል አቅም በማስቀመጥ ፣ በየአመቱ አዲስ ተማሪዎች የመቀበል አቅም በወቅቱ ያሳውቃል ፣

ለ/ በየዓመቱ ለሚመደቡ ተማሪዎች ኦረንቴሽን ይሰጣሉ፣

ሐ/ በየዩኒቨርሲቲዎች የተመደቡትን ተማሪዎች በተመደቡበት የትምህርት የመስክ ዙሪያ በየትምህርት ዓይነቱና በዲፓርትመንት /ፕሮግራም/ ይደለድላሉ፣

መ/ ከተማሪዎች ምደባ በኋላ በተማሪዎች ለሚነሱ የተለያዩ ችግሮች መፍትሔ ይሰጣሉ፣



ሳሙኤል ክፍሌ ኪዳኔ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ሠ/ በተማሪዎች የሚነሱ አሳማኝ የዝውውር ጥያቄዎች የሚፈታው በተመደቡበት ዩኒቨርስቲ አንድ ዓመት ተምረው ውጤት ከያዙ በኋላ በሚመለከታቸው ዩኒቨርስቲዎች መካከል በሚደረግ ቀጥተኛ ግንኙነትና ስምምነት መሠረት ዝውውር ይፈጸማል፡፡

13.3 ክልልና ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች፣

ሀ/ በስራቸው ላሉ ዞኖች፣ ወረዳዎችና ትምህርት ቤቶች በየደረጃው መመሪያውን ያሰራጫሉ፣ ያስተዋውቃሉ፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላሉ፣ መመሪያውን በሚጥሱት ላይ የእርምት እርምጃ ይወስዳሉ፣

ለ/ ከትምህርት ሚኒስቴር የሚላክ የአጠቃቀም ማኑዋልና ለእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የተዘጋጀው የተማሪዎች መረጃ መመዝገቢያ ድህረ ገፅ የይለፍ ቃል (ለዚህ መመሪያ ማስፈፀሚያ) በሁሉም መሰናዶ ትምህርት ቤቶች መድረሱን ያረጋግጣሉ፣

ሐ/ እያንዳንዱ የመሰናዶ ትምህርት ቤት መረጃውን በተሰጠው ፎርማት በትክክል ሞልቶ ማጠናቀቁንና የእያንዳንዱ ተማሪ መረጃ በድረ ገፅ በጊዜ ገደቡ መሠረት መላኩን በመከታተል ያረጋግጣሉ፣

መ/ የትምህርት ቤት ርእሳነ መምህራን የሚመለከታቸውን ክፍሎች፣ ተማሪዎችና ወላጆች መመሪያውን በአግባቡ እንዲያውቁት በማድረግ ተገቢውን እንዲፈጽሙ ድጋፍ ይሰጣሉ፣

ሠ/ በመረጃ አሰባሰብ ላይ የተለያዩ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ክፍተት እንዳይኖር በየደረጃው ተገቢው ድጋፍ ይሰጣሉ፣ ያስፈጽማሉ፣

13.4 የሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ፣



ሳሙኤል ክፍሌ ኪዳኔ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ሀ/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መግቢያ የመቁረጫ ነጥብ አማራጮችን የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመቀበል አቅምና የየዘመኑን የተማሪዎች ውጤት ግምት ውስጥ በማስገባት አዘጋጅቶ ለውሳኔ ያቀርባል፡፡

ለ/ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመቀበል አቅም፣ የትምህርት መስክና የተቋም ምርጫ መረጃና ውጤት በማሰባሰብ የተማሪዎችን ምደባ ያካሂዳል፡፡

ሐ/ የተጠቃለለና ውሳኔ ያገኘ የመጨረሻ የተማሪዎችን ምደባ በመንግሥት መገናኛ ብዙሃን ፣ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችና ቴክኖሎጂ በመጠቀም ያስታውቃል፡፡

መ/ ምደባን በተመለከተ የሚቀርቡ አስተያየቶች፣ አቤቱታዎች በመቀበል ያስተናግዳል ተገቢውንም መፍትሔ ይሰጣል፡፡

ሠ/ የምደባውን ስራ የተቀላጠፈና ተደራሽ ለማድረግና የደንበኞችን እርካታ የሚጨምሩ አሰራሮችን በየጊዜው እያጠና ያሻሽላል፡፡

ረ/ የተማሪዎች መረጃ መሰብሰቢያ ድህረ ገፅና የይለፍ ቃል ትምህርት ቤቶች እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡

13.5 ትምህርት ቤት፣

ማንኛውም የመሰናዶ ት/ቤት

ሀ/ የተማሪዎች የትምህርት መስክና የተቋም መምረጫ ቅጽ /ፎርም/ ላይ ከመሙላታቸው በፊት ስለትምህርት መስክና ተቋም አመራረጥ ለተማሪዎች በቂ ገለፃ በመስጠት ተማሪዎች ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ያደርጋል፡፡

ለ/ የተማሪዎችን መረጃ የዩኒቨርስቲና የስልጠና መስክ ምርጫቸውን ከምርጫ ፎርም ላይ በድህረ ገፅ በጥንቃቄ ያስገባል፡፡



ሳሙኤል ክፍሌ ኪዳኔ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ሐ/ በድህረ ገጽ የገባውን መረጃ በማተም ስለ ትክክለኛነቱ ተማሪዎች የየራሳቸውን ምርጫ አረጋግጠው እንዲፈሩሙበት በማድረግ በመረጃነት ይይዛል፡፡

መ/ የትምህርት ቤቱን ተማሪዎች የዩኒቨርስቲና የስልጠና መስክ ምርጫቸውን ለሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ በዌብሳይት ይልካል፡፡

ሠ/ ተጨማሪ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የህክምና ጉዳዮች እና የአካል ጉዳተኞች (በፎቶግራፍ የተደገፈ) እንደዚሁም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች መረጃን በጥንቃቄ በማደራጀት ለምደባ እንዲያገለግሉ ከምደባው 15 ተከታታይ ቀናት በፊት ለሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ ይልካል፡፡

ረ/ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ትክክለኛ የተማሪዎች መረጃ መላኩን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ከምደባ በፊት የሚያጋጥሙ የመረጃ ክፍተቶችን በማስተካከል ከሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

ሰ/ ተማሪዎች የተመደቡበትን ዩኒቨርስቲ ከድህረ ገፅ በማተም ተማሪዎች በግልፅ ሊያዩት በሚችሉበት ቦታ በመለጠፍ እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡

13.6 ተማሪ/አመልካች፣

ሀ/ ማናቸውም ተማሪ/ አመልካች/ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ የመስጠትና የመሙላት ኃላፊነት አለበት፡፡ በሀሰት መረጃ የተገኘ ምደባ በማናቸውም ጊዜ ሲታወቅ እንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡

ለ/ ተማሪዎች ምርጫቸውን እራሳቸው ወይም በህጋዊ ወኪሎቻቸው አማካኝነት በጥንቃቄ መሙላት ይኖርባቸዋል፡፡



ሳሙኤል ክፍሌ ኪዳኔ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ሐ/ በተማሪዎች የትምህርት መስክና የተቋም መምረጫ ቅጽ /ፎርም/ ላይ የሞላውና በድረገፅ የተላለፈው አንድ አይነት መሆኑን በማየት ስለትክክለኛነቱ በፊርማው ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

መ/ ለምደባ የትምህርት መስክና የተቋም መምረጫ ቅጽ /ፎርም/ ያልሞላ እና በድረገፅ ያልተላለፈለት ተማሪ በምደባው አይካተትም፡፡

ሠ/ የተመደበበት ዩኒቨርስቲ በትክክል የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡ የተመደበበት ዩኒቨርስቲ በትክክል ሳይለይ ቀርቶ ምዝገባ ጊዜ ሳይቀርብ ቢቀር ምደባውን በራሱ እንደሰረዘ ይቆጠራል፡፡

ረ/ በተመደበበት ዓመት ትምህርቱን ያልጀመረ ተማሪ በቀጣዩ ዓመት ሊመደብ አይችልም፡፡

ሰ/ ዩኒቨርስቲዎች በመገናኛ ብዙሃን በሚያስተላልፉት ጥሪ መሰረት እየቀረቡ መመዝገብ ይኖርባቸዋል፡፡ ከአቅም በላይ የሆነ ነገር ሲያጋጥማቸው በህጋዊ ወኪሎቻቸው ለተቋሙ /ለዩኒቨርስቲው/ ስለሁኔታው በማሳወቅ ከተቋሙ ጋር መፍትሄ ይፈልጋሉ፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

14. ማንኛውም ተማሪ ወደ መንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመግባት አንድ ጊዜ ብቻ የምደባ ዕድል እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ከምደባ በኋላ ከአቅም በላይ በሆኑ ችግሮች ምክንያት ትምህርታቸው መከታተል ባለመቻላቸው ለተመደቡበት ዩኒቨርስቲ በሚያቀርቡት አቤቱታ መሰረትና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ባላቸው ህግና ደንብ ብቻ የሚስተናገዱ ሲሆን ለሁለተኛ ግዜ የምደባ ጥያቄ ሊያቀርቡ አይችሉም፡፡



ሳሙኤል ክፍሌ ኪዳኔ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

15.አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች /በዊልቸርና በሁለት ክራንች የሚንቀሳቀሱ / የጉዳቱን አይነት የሚያሳይ ፎቶግራፍ ለትምህርት ቤቱ በማቅረብ ትምህርት ቤቱ ከድጋፍ ደብዳቤ ጋር በርዕሰ መምህሩ ተረጋግጦና ተፈርሞ በአድራሻ ለሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ ውጤት በተገለፀ ባሉት ተከታታይ 15 ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

16.ተማሪዎች ለምደባ የሚያበቃቸውን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግቢያ የብቃት መመዘኛ ፈተና ውጤት ሆኖ የዘመኑ መቁረጫ ነጥቡን ያሟሉ ይሆናሉ፡፡

17.ተማሪዎች በተፈጥሮ ሳይንስና ማህበራዊ ሳይንስ መስኮች ተለይተው የተዘጋጁ የትምህርት መስኮች በመለየትና በየትኞቹ ተቋሞች እንደሚገኙ ተገቢውን መግለጫ በማግኘት ዩኒቨርስቲዎችን በቅደም ተከተል እንዲመርጡ ይደረጋል፡፡

18.ለሴቶች፣ ለዓይነሥውራንና መስማት ለተሳናቸው፣ የታዳጊ ክልል፣ አርብቶ አደርና የከፊል አርብቶ አደር ተወላጅ የሆኑ ተማሪዎች /አመልካቾች/ የመቁረጫ ነጥብ ከሌሎች ተማሪዎች በተለየ ሁኔታ በሚኒስትሩ የሚወሰን ይሆናል፡፡

19.ለሴት አመልካቾች በውጤታቸው ከወንዶች ጋር ተወዳድረው ከሚያገኙት በተጨማሪ በማዕከል በትምህርት መስክ በአንደኛ ምርጫቸው በየአመቱ በትምህርት ሚኒስቴር በሚወሰነው መጠን በእርስ በርስ ውድድር ይመደባሉ፡፡

20.አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ከ1ኛ-3ኛ የተቋም ምርጫቸውን ይጠበቅላቸዋል፡፡

21.የታዳጊ (አፋር፣ ኢትዮጵያ ሱማሌ፣ ቤኒሻንጉልና ጋምቤላ) ክልል ተማሪዎች በውጤታቸው ከሌሎች ጋር ተወዳድረው ከሚያገኙት በተጨማሪ በማዕከል በትምህርት መስክ የየአመቱን ውጤት መሠረት በማድረግ በተለየ ትኩረት እንዲስተናገዱ በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ይወሰናል፡፡

22.ተጨባጭ መረጃ በማቅረብ በአንድ ተቋም ለመመደብ ጥያቄ ሲያቀርቡ ያታቸው አንድ አይነት የሆኑ መንትዮች እንዲስተናገዱ ይደረጋል፡፡ በትምህርት ውጤታቸው



ሳሙኤል ክፍሌ ኪዳኔ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Education

መሰረት በሚደረግ ውድድር ከሁለቱ የተሻለ ውጤት ያላት/ያለው ተማሪ በተመደበችው/ው ቦታ ላይ ሁለቱም በአንድ ተቋም እንዲመደቡ ይደረጋል፡፡

23.በማንኛውም ወቅት በመንግሥት የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተመድበው በተለያየ ምክንያት ትምህርታቸውን ያቋረጡ ተማሪዎች ጉዳያቸው የሚታየው ቀደም ብሎ በተመደቡበት ተቋም ብቻ ይሆናል፡፡

24. በምደባ ወቅት የእርስ በርስ ቅይይርና ዝውውር መፈፀም አይቻልም፡፡

25.ልጅ የሚያጠቡ ተማሪዎች በአቅራቢያቸው በሚገኘው ዩኒቨርስቲ ለመመደብ ጥያቄ ሲያቀርቡና መረጃው ውጤት በተገለፀ ባሉት 15 ተከታታይ ቀናት ውስጥ በትምህርት ቤት በኩል ከቀረበ በጠየቁት ዩኒቨርስቲ ሊመደቡ ይችላሉ፡

26.የቅሬታ አቀራብ ሥርዓት፣

26.1 ማንኛውም ለምደባ ብቁ የሆነ ተማሪ በትምህርት መስክና ተቋም ምደባ ስህተት ወይም በምደባ በቅበላ ወቅት አወንታዊ ድጋፍ የሚደረግለት ሳይደረግለት ቢቀር ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

26.2 ከላይ በንዑስ ተራ ቁጥር 24.1 ላይ የተጠቀሰው ቅሬታ መቅረብ ያለበት ምደባ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ15 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ብቻ ነው፤ ቅሬታውም በአካል፣ በውክልና፣ በስልክ፣ በፋክስ፣ በኢሜልና በትምህርት ጽ/ቤቶች በኩል ሊቀርብ ይችላል፡፡

26.3 በቀረቡ ቅሬታዎች ላይ ከ10 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ምላሽ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

26.4 ከላይ በንዑስ ተራ ቁጥር 24.3 መሠረት ከኤጀንሲው በተሰጠው ምላሽ ቅሬታ ያለው ወገን ቅሬታውን ለትምህርት ሚኒስቴር ማቅረብ ይችላል፤

26.5 ከምደባ በኋላ የሚቀርብ ማንኛውም ማስረጃ ተቀባይነት የለውም፡፡



ሳሙኤል ክፍሌ ኪዳኔ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

26.6 ትምህርት ቤቶች፣ ዩኒቨርሲቲዎች እና የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ በጎና አስቸጋሪ ሁኔታዎች ለክልላቸው ትምህርት ቢሮና ለሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

## 27. መመሪያውን ስለማክበር

በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በማንኛውም ሁኔታ የጣሰ፣ እንዲጣስ ያደረገ ማንኛውም በየደረጃው ያለ አስፈጻሚና ፈፃሚ አካል በአገሪቱ ባሉ ህጎች፣ ደንቦችና አስተዳደራዊ እርምጃዎች መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 28. መመሪያው ሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ፣

ይህ መመሪያ ከነሃሴ 8 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

-----------------------------------------------------------

ጥላዬ ጌቴ (ዶ/ር )

የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር